የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፮
አዲስ አበባ–ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 56
ADDIS ABABA - 7th July, 1998

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፱/፲፱፻፺ ዓ.ም.
የጥሪት ፈንድ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................................... ገጽ ፰፻

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 39/1998
Sinking Fund Establishment Council of Ministers Regulations ........................................ Page 800

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፱/፲፱፻፺

## የጥሪት ፈንድ ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፶፯/፲፱፻፹፱ አንቀጽ ፵፯ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የጥሪት ፈንድ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፱/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· የጥሪት ፈንድ ስለመቋቋሙ

የጥሪት ፈንድ (ከዚህ በኋላ "ፈንዱ" እየተባለ የሚጠራ) የገንዘብ ሚኒስቴር በሚከፍተው ልዩ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ተቀማጭ እንዲሆን በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፫· የፈንዱ ምንጮች

፩· በየበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው የመደበኛ በጀት፣ የካፒታል በጀት፣ እንዲሁም ከተፈቀደው የክልሎች ድጎማ የግምጃ ቤት ድርሻ ከሆነውና በበጀት ዓመቱና በተሰጠውም የችሮታ ጊዜ ውስጥ ሥራ ላይ ሳይውል የቀረው፣

፪· ከዕቅድ በላይ የተገኘ ገቢ ፤

ይሆናል ።

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 39/1998

### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF SINKING FUND*

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47 of the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No. 57/1997.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Sinking Fund Establishment Council of Ministers Regulations No.39/1998."

2. *Establishment*

The Sinking Fund (hereinafter "the Fund") is hereby established to be deposited in a special account to be opened by the Ministry of Finance.

3. *Sources of the Fund*

The Fund shall be collected from the following sources:

1) Recurrent and capital budgets, as well as share of the treasury from subsidy budget of the Regions, approved every fiscal year and not utilized within the fiscal year or the grace period;
2) Revenue collected over and above the forecast.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፬· <u>የፈንዱ ዓላማ</u>

የጥሪት ፈንዱ ፤

፩· በረጅም ጊዜ እንዲከፈል የተወሰደን ብድር ለመክፈል፤

፪· ለቋሚ ንብረቶች መተኪያ ፤

፫· የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሚወስንባቸው ሌሎች ጉዳዮች፤

የሚውል ይሆናል።

፭· <u>ስለክፍያዎች</u>

ከፈንዱ ሂሳብ ገንዘብ ወጪ ሆኖ የሚከፈለው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፈቅድ ይሆናል።

፮· <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ ፤

፩· ፈንዱ የሚቀመጥበትን ልዩ የባንክ ሂሳብ ይከፍታል ፤

፪· ከተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ወደዚህ ፈንድ ገቢ የሚደረገውን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ የተመለከተውን ገንዘብ ወደፈንዱ የባንክ ሂሳብ ያስተላልፋል ፤

፫· የፈንዱን ሂሳብ ይይዛል፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣ ያስተዳድራል።

፯· <u>መዝገቦች እና ሂሳቦች</u>

የፈንዱ የመዝገብና የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን የሚከተል ይሆናል።

፰· <u>ኦዲት</u>

የፈንዱ ሂሣብ በዋናው ኦዲተር ይመረመራል።

፱· <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

4. *Objectives of the Fund*

The Objectives of the Fund shall be:

1) to repay long-term debt;
2) to replace fixed assets; and
3) to any other public purpose determined by the Council of Ministers.

5. *Disbursement*

Disbursement of the Fund shall only be made with prior authorization of the Council of Ministers.

6. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to:

1) open a special account for the deposit of the Fund;
2) transfer from the consolidated fund into the Fund's special account the amount specified under Article 3 of these Regualtions;
3) maintain and administer the Fund's special account, make disbursements out of the special account for expenditures authorized by the Council of Ministers.

7. *Records and Accounts*

The records and accounts of the fund shall be maintained in accordance with the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation.

8. *Audit*

The accounts of the Fund shall be audited by the Auditor General.

9. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 7th day of July, 1998.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC

OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE